# ቤተ ክርስቲያንና ተከታዮቿ

ሰላማ ቁጥር ፰ ፲፱፻፹፰/1986

ከመርዓዊ ተበጀ

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ያልደረሱበት ክፍለ ዓለም አይገኝም። በቅርቡ አንድ የጥናት ሰው እንደተናገሩት በአላስካና በአውስትራልያ ኢትዮጵያውያን ይገኛሉ። በሥጋዊ ኑሮአቸው ከነባሩ ሕዝብ ጋር መቀላቀል የሚከብዳቸውን ያህል በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም የበለጠ ችግር እንዳለባቸው በየቦታው እየተገለጸ በመሄድ ላይ ነው።

ከቅዱስ ሲኖዶስ በቅርቡ የወጣው መግለጫ እንደሚያመለክተው በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ አገልገሎት የሚሰጡ ሁለት መቶ አምሳ ሺህ (250.OOO) ካህናት ይገኛሉ። ታዲያ ይህን ያህል የካህናት ቁጥር ያላት ቤተ ክርስቲያን ካህናት ልጆቿን በሐዋርያነት ሙያ አሠልጥና ወደ ውጭ ለመላክ ያደረገችው ጥረት የለም ብንል ከስህተት አይቆጠርም። በአንጻሩ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው በየክፍላተ ዓለሙ የተበታተኑት ምእመናን መንፈሳዊ አገልግሎት ማለት በዕለት ኑሮአቸው የሚናዝዛቸውና የሚያጽናናቸው፤ ልጆች ሲወልዱ ጥምቀተ ክርስትና የሚፈጽምላቸው፤ ለወጣቶች ሥርዓተ ተክሊል የሚያደርስላቸው፤ በዕለተ ሞት ጸሎተ ፍትሐት የሚያደርግላቸው፤ አስተምሮና አሳምኖ የእግዚአብሔር ልጅ የሚያደርጋቸው፤ ቀድሶ የሚያቆርባቸው ካህን ለማግኘት ያደረጉት አስተዋጽኦ ምን አለ? ብሎ መጠየቅም አስፈላጊ ነው። በእርግጥ የሚቀርብ አንዳንድ ምክንያት ይኖራል። በየቦታው ተበታትኖ መኖር፤ የሀገሩ እንግዳ፤ የሕዝቡ ባዕዳ መሆን፤ ከላይ የተገለጹትን ለመፈጸምና ለማስፈጸም አያስችልም የሚል መላ ምት እናቀርብ ይሆናል። ለሁሉም ግልጽ የሆነው ግን ጌታ በማቴዎስ ወንጌል በም. ፲፰ በቁ.፲፱ እና ፳ ላይ „ እውነት እላችኋለሁ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ።“ ብሎ የተናገረውን አምላካዊ መመሪያ ከልብ ማስተዋሉ እጅግ ጠቃሚ ነው። በክርስቶስ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በየትም ቦታ ሁለት ወይም ሦስት ቢሆንም፤ ሕያው የሆነው የክርስቶስ መመሪያ እንደማይለየው ማመን ይገባል። እንዲህም ከሆነ የራስን ማኅበረ ክርስቲያን መመሥረት፤ የጸሎት ቤት ማቋቋም ይገባል ማለት ነው። ለአምልኮተ እግዚአብሔር የተወሰነ ቦታ የለውም። እግዚአብሔር በዓለሙ ሁሉ ሙሉ ነው። ከዚህ አለ፤ ከዚያ የለም አይባልም፤ ይህም በመሆኑ ነው ማኅበረ ክርስቲያን መመሥረት፤ ጸሎት ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሁኖ የተገኘው።



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ያለው ሕዝብ ወደ ሌላው በመወሰድ ሳይሆን፤ በየትኛውም ቦታና ሰዓት የራሱን እምነት፤ ባህልና ልማድ መጠበቅ ይኖርበታል። ለሰው አንድ አባትና አንዲት እናት፤ አንድ ሀገርም ያለውን ያህል አንድ ሃይማኖትም ሊኖረው ይገባል። የእንጀራ ባትና እናት፤ የስደት ሀገር፤ በሌላም ሃይማኖት መበረዝ የለም ማለት ሳይሆን፤ የሥጋና የመንፈስ እርካታ፤ የኀሊና ክብር የሚሰጠው የራስ ብቻ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው።

ከዕለታዊው የመንፈሳዊ አገልግሎት ሥራችን ልምድ በመነሣት እንደምንረዳው፤ አንዳንድ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሌላ ክርስቶስ፤ ልዩ መንግሥተ ሰማያት ያለ ይመስል፤ „ያጸድቁናል“ ብለው ሳይሆን „ይረዱናል“ በሚል ሰበብ ሃይማኖታቸውን የተውና የለወጡ፤ ሕልውናቸውን የረሱ፤ ከወላጆቻቸው ትውፊት የኮበለሉ እንዳሉ ልንጠቁም እንወዳለን።

በሰሜንና በመካከለኛው አውሮፓ የተበታተነው ሕዝብ በያለበት ቢዘጋጅ፤ በሀገራችን ከአንድ አጥቢያ /ሰበካ/ ቤተ ክርስቲያን፤ ከአንድ ጎጥና ጢስ አያንስም። ለምሳሌ በግሪክ፤ በኢጣሊያ፤ በፈረንሳይ፤ በቤልጅግ፤ በሆላንድ፤ በስዊዘርላንድ፤ በዴንማርክ፤ በስዊድንና በኖርዌይ ያለው ሕዝበ ክርስቲያን ቁጥሩ እጅግ ብዙ ነው። ግን እስካሁን የተቋቋመ አንድም ማኅበረ ክርስቲያን የለም። ለዚህም ምክንያቱ ብዙ ነው። አገልጋዩ ክፍል ተዘጋጅቶ የፈለገኝ የለም ሲል፤ ተገልጋዩ ደግሞ እኔን ለማገልገል የተዘጋጀ የለም ይላል። አንዱ በአንዱ እያመካኘ ዕለታት እየተቆጠሩ፤ ዘመናትም እያለፉ ናቸው። ነጣቂ ተኩላ እንዳይበላን ጸልዩልን የሚለውም ቁጥሩ የተወሰነ ነው።

በእንግሊዝና በምዕራብ ጀርመን የተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፤ ነገር ግን ከአገልጋዮች እጥረት፤ ከሕዝበ ክርስቲያኑም ዝግጅት ጉድለት የተነሣ፤ በየቦታው በቂ አገልግሎት መስጠት አልተቻለም።

በእርግጥ እኛ ኢትዮጵያውያን በብዛት በውጭ ሀገር ተበታትነን ስንኖር ፳ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻችን ሳይሆን መጀመሪያችን ነው። አንዳንዶቻችን ከፍካሬ ኢየሱስ „በዚያን ጊዜ ጦርን የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ሕዝብ በሕዝብ ላይ፤ መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣልና ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል። እርስ በእርሳቸው አሳልፈው ይሰጣጣሉ። እርስ በእርሳቸውም ይጣላሉ። ከአመጽም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።“ (ማቴ.፳፬.፮-፲፫) በመጥቀስ የዓለሙ ፍጻሜ እንደደረሰ ብንተነብይም አንዳንዶቻችን ደግሞ „ ያችን ቀን የሚያውቃት ማንም የለም“ (ማቴ.፳፬.፴፮) የሚለውን ቃል ብናብራራም፤ ለሁሉም ማጠቃለያው „ ድልዋኒ ክሙ ንበሩ“ (ማቴ.፳፬. ፵፬) ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሚለው አምላካዊ ትእዛዝ ነው። ዝግጅት ለዛሬ፤ ዝግጅት ለነገ፤ ዝግጅት ለነገ ወዲያ፤ ዝግጅት በትውልድ ሀገር፤ ዝግጅት በባዕድ ሀገር ያስፈልጋል።

ይሁን እንጅ ሃይማኖትን ከፖለቲካና ከብሔረ ስብእ ጥያቄ ጋር በማገናኘት የሚደረገውን የመንፈሳዊ ሕይወት እንቅስቃሴ አንድነት ለማሰናከል የሚደረግ ሙከራ አለ። የዚህ ዓይነቱ ሙከራ ጤፍን ከአሸዋ፤ ስንዴን ከእንክርዳድ ጋር ቀላቅሎ እንደመፍጨት ያስቆጥራል። ሃይማኖት ወሰን እንዲሁም ደንበር የለውም፤ እንዲሁም ደህም ተያን የሁሉ ናት። በአንዲት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተጠመቀ ክርስቲያን በጎሳ ወይም በጾታ፤ በዘር ወይም በነገድ፤ በባህል ወይም በቋንቋ አይለይም። ሁሉም የአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጅ ነው። (፫፻፲፰ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን „በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።“ ብለው በጸሎተ ሃይማኖት እንደደነገጉ ልብ ብሎ ይመለከቷል።)

ከግብጻውያን፤ ከባቢሎናውያን፤ ከግሪካውያንና ከሮማውያን ቅኝ ገዥዎች ጋር በመታገል በስደት ኑሮ የታወቁት እስራኤላውያን ሃይማኖታቸውንና ልማዳቸውን በመጠበቃቸው ከእልፍ አእላፋት አሕዛብ መካከል ማንነታቸውን ሊያሳውቁ ችለዋል። አንድ ሕዝብ በብሔራዊነቱ የሚታወቀውን ያህል በሃይማኖቱም ይታወቃል። ሌላም ምሳሌ በተጨማሪ ለመጥቀስ ያህል ለ፭፻ መቶ (500) ዓመታት በቱርክ ኦስማን መንግሥት ሲቀጠቀጡ የኖሩት የግሪክ፤ የሩማንያ፤ የቡልጋሪያ፤ የዩጎዝላቪያ እንዲሁም ለ፪፻፶ (250) ዓመታት በታታር መንጎላውያን ሲሰቃዩ የነበሩት የሩሲያ ሕዝቦች ከኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸው ሊናወጡ አልቻሉም። የግብጽ፤ የአርመን፤ የሶርያና የሕንድ ኦርቶዶክሳውያንም ከሰማዕትነት ጋር የተዋሐደ የሃይማኖት ታሪክ አላቸው። በዓረቦችና በቱርኮች እንዲሁም በምዕራባውያን የተፈጸመባቸው ግፍ ቁጥራቸውን ቢቀንሰውም፤ ዓላማቸው ሕያው ነው። ትብብራቸውም የሐውልት ምስክር ነው። የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እምነት ተከታዮች በየትኛውም ክፍለ ዓለም ይገኛሉ። በአንጻሩም የራሳቸው ማኅበረ ክርስቲያንና ቤተ እግዚአብሔር አላቸው። የእኛ የለንም ለማለት አይደለም፤ በአሁኑ ጊዜ በሱዳን፤ በጅቡቲ፤ በኬንያ፤ በትሪኒዳድና በጃማይካ በአሜሪካና በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮችና አያሌ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። ከላይ እንደተገለጸው ለሃይማኖት ወሰንና ደንበር፤ የጎሣና የጾታ፤ የዘርና የነገድ፤ የቋንቋም ልዩነት ስለሌለው ሕዝብና አሕዛብ፤ ነጭና ጥቁር የቤተ ክርስቲያን አባሎች ናቸው።

ሌላው ደግሞ ከዚህ ለየት ያለ ነው። የካቶሊክና የፕሮቴስታንት፤ በአጠቃላይም የቅኝ ገዥዎች እምነት ተከታዮች ጥቁር አሜሪካውያንና አፍሪካውያን ቤተ ክርስቲያናቸውን „የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን“ ብለው የሚጠሩ ሲኖሩ፤ የአክሱም ጽዮንንም ታሪክ የተረዱ „የኢትዮጵያ ጽዮን“ ብለው ሰይመውታል። ለሰው ልጅ መብት ተከራካሪ የሆኑት የአሜሪካ ጥቁሮችም በኒውዮርክ የአቢሲንያ ቤተ ክርስቲያን (ካቴድራል) ሰባኪዎች ናቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆኑ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም የሚጠሩት ወገኖች ለእነርሱ አንድ ልዩ ታሪክ አለው፤ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ነፃነትና ልዩ ታሪክ፤ በሌሎች ያልተከለሰውና ያልተበረዘው፤ በዓረቦች ኃይል ያልጠፋው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እምነት ለእነርሱ አንድ መመኪያ ነው። ለእኛስ? „በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ እኩል ነው“ እንደሚባለው ካልሆነ በስተቀር ሃይማኖታችንን በብዙ መሥዋዕትነት ላቆዩልን አባቶች ትችት ልናቀርብ አንችልም። ነገር ግን ጥያቄ ማንሳት የምንችልበት አንድ የተውልድ

ዘመን ይኖራል። ይኸውም የ፶ ዓመት ታሪክ ይኖረዋል። መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ የተባሉ ምሁር „ውላጤ ዘእንበለ ውላጤ“ ለውጥ ያለ ለውጥ በሚል የመንደርደሪያ ሐሳባቸው በ፳ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የነበሩትን የኢትዮጵያን የምንስትሮችንና የጀኔራሎችን ቤት ከተመለከቱ በኋላ „ቤታቸው ጸበል ከተረጨ ፴ ዓመት ሁኖታል“ ይሉ ነበር። የወጣቱ ትውልድ መንፈስም መሸርሸሩንና መበረዙን አይተው፤ አንድ ገበሬ እህል አለኝ እያለ፤ እየተበደረ ከበላ በኋላ፤ የራሱን ክምር አይቶ „አንቺ ክምር ያለሁ ይመስልሻል? ተበልተሽ አልቀሻል።“ ብሎ የትናገርውን መላልሰው ይናገሩ ስለነበር፤ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። የዘመናችን ደራሲ አቶ አዲስ ዓለማየሁ „ወንጀለኛው ዳኛ“ በሚለው መጽሐፋቸው ስለነበረው ሥርዓተ ማኅበርና ጽኑዕ ሃይማኖት ከገለጡ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን አስተያየት አቅርበዋል።(የፊደል አቀማመጡ ደራሲው እንዳስቀመጡት ነው። ላላስተዋለው ስህተት ያለበት መስሎ ይታያል) „...ምንም እንኩዋ ኢትዮጵያ ከ፲፱፻፳፰-፲፱፻፴፫፤ ላምስት አመታት ብቻ በፋሽሽት ኢጣልያ ከመወረርዋ በቀር በሌሎች ያፍሪቃ አገሮች የደረሰው፤ በቅኝ ገዥዎች ለረዥም ጊዜ የመገዛት ክፉ እድል አልገጠማትም። ገዥዎችዎችዋ ቸው በልማት ወደ ሁዋላ የቀረች በመሆንዋ አውሮፓውያን፤ ወይም ባጠቃላይ ፈረንጆች በደረሱበት የልማት ደረጃ ቶሎ እንድትደርስ እነሱ የሚሰጡትን ትምህርትና ምክር፤ ስራታቸውን ጭምር መቀበል ያስፈጋል ብለው በማመን ለፈረንጆች በፈቃዳቸው በራቸውን በሰፊው መክፈት ብቻ ሳይሆን በብዙ መንገድ የፈረንጆችን ስራት ተቀብሎ መከተል ያዋቂነትና የስልጡንነት ምልክት ፤ የኢትዮጵያን የቆየ ስራት ተቀብሎ እንደያዙ መቆየት የሁዋላ ቅርነት ምልክት ሁኖ እንዲታይ ያደፋፍሩ ስለነበር በተለይ በከተማ የፈረንጆች ስራት የኢትዮጵያን የቆየ ስራት እየገፋ ቦታ ማስለቀቅ ከጀመረ ቆየት ብሎዋል። ነገር ግን ጥንታዊው የኢትዮጵያ ስራት ቦታው ለባእዱ ስራት እንዲያስረክብ በህግ የተፈረደበት ከፋሽሽት ኢጣልያ ወረራ በሁዋላ ነው።“ የሁለቱም ምሁራን አነጋገር እውነትነት አለው። ዘመናዊና ሥልጡን በሚል ልባስ ነባራዊው ልማድ ያለው ያልተማረና ያልሠለጠነ፤ በውጭ መንፈስ የተካነው ደግሞ የሠለጠነ፤ ሁሉን አዋቂና መርማሪ መስሎ የታየበት ጊዜ እንደነበር፤ ልንዘነጋ አይገባንም። አሁንም ሙሉ በሙሉ ቅርቷል ማለት አይቻልም።

እንግዲህ ከሀገሩ የወጣው አብዛኛው የዚህ መንፈስ የነበረውና ያለው ነው። ከሀገሩ ይዞት የወጣው መንፈሳዊና ባህላዊ ቅርስ በቂ ባለመሆኑ በሚሲዮናውያንና ባንዳንድ ነጋዴዎች የተጻፉትን መላልሶ ማንበብ ግድ ሁኖበታል። „አገራችን ሳለን የማናውቀውን አሁን አወቅን“ የሚለው ክፍል አንስተኛ አይደለም። የተጻፈው ሁሉ ለራስ በሚስማማ ዘዴ እንጂ፤ እውነተኛውን የሀገር ታሪክና የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ትምህርት የያዘ ባለመሆኑ ስህተቱ እጅግ ብዙ ው። እንዲያውም አንዳንዶቹ ጽሑፎች ዘመድን ከአዝማድ የሚለያዩ ናቸው።



<u>ማ ጠ ቃ ል ያ</u>

እንግዲህ ሊታሰብባቸው የሚገቡትን ነጥቦች በቅደም ተከተል አስቀምጣለሁ። ፩ኛ ሃይማኖታዊ ግዴታን ማሟላት

ሀ/ ጸሎት ቤት መክፈት

ለ/ቤተክርስቲያን ማቋቋም

ሐ/ ማኅበረ ክርስቲያን መመሥረት

፪ኛ ለማኅበዊ ኑሮ ዘርፍ ትኩረት መስጠት

ሀ/ መዋዕለ ሕፃናት መክፈት

ለ/ ለወጣቶች መሠረተ ትምህርት መስጠት

ሐ/ እርስ በእርስ መረዳዳት (የመረዳጃ ማኅበር ማቋቋም)

መ/ ራስን ለሥራ ማስገዛት (በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ ኦሪት ዘፍ.ም.፫ ቁ. ፲፱)

ለ/ ትምህርት መማር፤ ሳይንሳዊ ምርምር ማድረግ፤

አንባቢዎች! ሁኔታውንስ ደረ ደርከው፤ ግን በሥራ እን ዴት ይገለጣል የሚል ጥያቄ ማቅረባችሁ አይቀርም። እር ግጥ በአውሮፓ ራስን ለመ ቻል የሚደረገው ጥረት ዕድሉ እየጠበበ በመሄድ ላይ ነው። ከዕለት ወደ ዕለት የሚታየው ሁኔታ አስተማማኝ አይደለም። ከመካከላችን አብዛኛው የሚያዩ ዓየኖች፤ የሚሠሩ እጣቶች፤ የሚራመዱ እግሮች፤ እያሉት የቁም እስር ነው። ተቀባይ እንጂ አቀባይ፤ ተረጅ እንጂ ረጅ አይደለም። አንድ ሰብአዊ ፍጡር አዳማዊነቱን ሊያረጋግጥ የሚችለው መቀበልም ሆነ ማቀብል፤ መረዳትም ሆነ መርዳት፤ መሥራትም ሆነ ማሠራት፤ መታዘዝም ሆን ማዘዝ ሲችል ነው።

እስቲ እንግዲህ ከእስራኤላውያን ጋር ሁኖ ከዛሬ 2.600 ዓመት በፊት በፋርስ ባቢሎን የስደትን ችግር የቀመሰው ነቢዩ ኤርምያስ የሰጠውን ምክርና መመሪያ አብረን እናንበው ,,..... እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ ይላል.... ቤት ሠርታችሁ ተቀመጡ አትክልትም ተክላችሁ ፍሬዋን ብሉ፤ ተጋቡ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ውለዱ፤ ከዚያም ተባዙ፤ ጥቂቶችም አትሁኑ። በእርስዋ ሰላም፤ ሰላም ይሆንላችኋልና ወደ እርስዋ ላስማረከኋችሁ ከተማ ሰላምን ፈልጉ፤ ሰለእርስዋም ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ።“ ኤርም.ም.፳፱ ቁ.፬-፯